# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 18

ግንቦት 14 ቀን 2014ዓም (22-05-2022)

የጨነቀው ፍቅረኛ ስጋት በሰፈነበት እሩቅ ቦታ ለምትኖረው ለሚወዳት ኮረዳ ያለውን ስሜት እንዲህ ሲል ገልጾታል፣እቴ አከራረምሽ ኑሮሽ እንደምን ነው፣የኔስ ጭንቅ ሆኗል መላቅጥም የለው።አዎ የሚወዱት በሚኖርበት ቦታ ችግር ሲፈጠርና፣የሚሆነውን ሁሉ ሲሰሙ ያስጨንቃል።እኛም አገራችንና ወገናችንን ያሉበትን ኑሮ ስናስበውና ሁኔታውንም ስንከታተለው በቅጡ ያስጨንቀናል።መልካም ነገር ብንሰማና ብናይ ኖሮ ጭንቀታችንና ስጋታችን በደስታ በተቀዬረ ነበር።ላለፉት 50 ዓመታት በተለይም ላለፉት 31 ዓመታት ከዛም በባሰ ላለፉት 4 ዓመታት የሆነውና እዬሆነ ያለው ጉዞ ግን ከአቀበት ወደ ገደሉ፣ከድጡ ወደማጡ እንጂ ወደተሻለ አቅጣጫ አላመራም።ስለሆነም ስጋታችን ከቀን ወደቀን ጨምሯል እንጂ አልቀነሰም።ጭንቀታችን ሕዝባዊ አመጽ በመከሰቱ ሳይሆን አመጹ የተበታተነና የጠላቶቻችንን የተባበረ ክንድ ሊሰብር በሚችል ጠንካራ የጋራ ግንባር ባለመመራቱ ምክንያት ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ስናስበው ነው።ሃሳብና ጭንቀታችን የሚወገደው በጠንካራ አመራርና ሕዝባዊ ተሳትፎ የአገራችን አንድነቷና ሰላሟ ተጠብቆ፣ከገባችበት መቀመቅ ለመውጣት ስትችል፣ሕዝቧም ከጎሰኞችሥርዓትና አስተሳሰብ ነጻ ሲሆን፤ፍትሕና ዴሞክራሲ ሰፍኖ እንደ ዜጋ ተከባብሮ መኖር ሲቻል ነው።

የአገራችንን አደገኛ ጉዞ ሁሉም አገር ወዳዶች ሲከታተሉትና ሲያስጠነቅቁ ኖረዋል፤መፍትሔዎችንም ለመጠቆም ሞክረዋል።ከዛም አልፈው ተርፈው የፍርሃትን ድባብ ሰብረው የቀውሱ ባለቤት የሆነውን ስርዓት ለመፋለም ነፍጥ አንግበውየህይወት ዋጋ የከፈሉ ብዙዎች ናቸው።አሁንም በዚያው ትግል የተሰለፉ ሕዝባዊ ሃይሎች ፣ፋኖዎች በመበራከት ላይ ናቸው።ከጠላት ጋር የሚደረገው ግብ ግብ ከቃላት አልፎ የሞትና የሽረት፣ በጥይት የታጀበ ሆኗል።እኛም የዚህ ሕዝባዊ ትግል ደጋፊዎች ነን።

በመላ አገሪቷ በተለይም በአማራው አካባቢ የሚደረገው በሥርዓቱ የተቀናጀ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻና በቅጥረኞች ጫጫታ የታጀበ ወታደራዊ ጥቃት እርምጃ የሕዝቡን መነሳሳት ለማቆም ጥረት ቢደረግም ውጤቱ የተገላቢጦሽ ሆኗል።ሕዝቡ የተጫነውን የፍርሃት ድባብ ሰብሮና፣የከለለውን ዳፍንት ወይም አዚም በማራገፍ በድፍረት ድምጹን ለማሰማት አደባባይ ላይ በመውጣት ላይ ነው።በባዶ ሜዳም ከመጮህ ባለፈ ጠላቶቹን በሚገባቸው ቋንቋ ለማናገር ከተሰለፉት ልጆቹ ከፋኖና ልዩሃይል ጋር እጅ ለእጅ ተያይዞ ለትግሉ ቆርጦ መነሳቱን ይፋ አድርጓል።ይህ ሕዝባዊ እምቢተኝነት ወደ ሕዝባዊ አመጽ ለመቀዬር የሚያስችሉ ምልክቶች እዚህና እዚያ እዬታዩ ነው።በተለይም በአማራው ክልል በተባለው የስርዓቱ አገራዊ ክፍል በሆነው ከሚታዬው ሕዝባዊ እንቅስቃሴና ተቃውሞ በተጨማሪ በአገሪቱ ዋና ከተማ በሆነችው በአዲስ አበባም ውስጥ የሕዝቡ ተቃውሞ በመቀጣጠል ላይ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ብቅ ብቅ ብለዋል።በተለይም የእብሪተኛው ባለተረኛ የኦነግ መራሹ ቡድን በትምህርት ቤቶች ውስጥ ሳይቀር የከተማዋና የአገሪቱ ባለቤትነቱን ለማሳዬት ሲል ባንዲራውን ባሻበት ቦታ የማንጠልጠሉን ድፍረት ተከትሎ የተነሳው የተማሪዎችና የወላጆች ተቃውሞ ለቀጣዩ ሕዝባዊ አገር አቀፍ አመጽ የማቀጣጠያ ክብሪትና ነዳጅ እንደሚሆን አንጠራጠርም።

ባለፈው ስርጭታችን እንዳሳዬነው በመሿለኪያ አካባቢ በሚገኘው ት/ቤት የኦነግን ባንዲራ የማንጠልጠልና የማይታወቅ የኦሮሙማ መዝሙር የማዘመር ግዳጅ ምክንያት በተነሳው ተቃውሞ ከደረሰበት ሃፍረትና ውድቀት ትምህርት ያልቀሰመው ጭፍን ቡድን ያንኑ የጨነገፈ ሙከራውን በየካ

አካባቢ በሚገኘ ት/ቤት ደግሞታል፤ሕዝቡም ነቅሎ በመውጣት በሚሊኪያ ያደረገውን ተቃውሞ በመድገም፤ባንዲራውንም ከተንጠለጠለበት እንጨት ላይ አሶርዶታል፤ልጆቹንም የማይታወቅ የቁቤ መዝሙር አይዘምሩም ብሎ ከትምህርት ቤት አስወጥቷል።ይህ ተቃውሞ በትምህርት ቤቱም ውስጥ ባሉ መምህራን መካከል ልዩነት የፈጠረ ሲሆን ተቃውሞ ባሳዩት መምህራንም ላይ ከሥራ የማገድ እርምጃ ተወስዶባቸዋል።ይህ በትምህርት ቤቶች ዙሪያ የተነሳ ተቃውሞ ለቀጣይ የከተማ ሕዝባዊ አመጽ የበኩሉን ጠጠር ወርውሯል ብለን እናምናለን።

ለከፋው ሰው ማጭድ አታውሰው እንደሚባለው ሁሉ የብዙ መከራ ሰለባ የሆነን፣በኑሮ ውድነት የሚጠበስና የሚሰቃይ፣በሰላም ውሎ መግባት የሚናፍቀው፣ሠርቶ ለማደር የሚሻ ግን ሥራና ዕድሉ በጎሳ ማንነት የሚያገኙት ሙብት በሆነበት፣በአምባገነኖች መዳፍ የሚዳሽቅ፣ከዛም አልፎ ተርፎ አገር ለማፈራረስ የሚዳክር ፣ እያሸበረ የፈለገውን የሚያደርግ እብሪተኛ፣ዘራፊና ሌባ ቡድን ሥልጣን በያዘበት አገር ውስጥ ሊከሰት የሚችለውን ሕዝባዊ አመጽ የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው።የግፍ ዋንጫው ሲሞላ ሕዝባዊ አመጽን ይወልዳል።ሕዝባዊ አመጽም በትክክለኛው ጎዳና ከተጓዘና ሃቀኛ መሪ ድርጅት ካገኘ እንደ ሱናሚ ከፊቱ የቆመውን የጠላት ሃይል ጠራርጎ ይወስዳል እንጂ የሚያቆመው አይኖርም። በዬቦታው በውጭና በአገር ውስጥ የሚገኙት የንቅናቄው ደጋፊዎች በአንድ ተሰባስበው መቆም ይኖርባቸዋል።በጎጥና በቡድን ተከፋፍሎ እርዳታ ማሰባሰቡ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፤ለመከፋፈልም በር ይከፍታል።

በአንድ አገር ውስጥ የሥርዓት ለውጥ ሊመጣ የሚችለው እንኳንስ ብዙሃኑን ባሳተፈ ይቅርና በአነስተኛ ቁጥር ባላቸው ወይም በግለሰብ ብሶትና በሚወስደው እርምጃ መሆኑን በሌሎች አገሮች በተለይም በቱኒዝያ ውስጥ በአንድ የመንገድ ላይ ነጋዴ ወጣት ስርዓቱ ባደረሰበት ተጽእኖ ባደረበት ብሶት ሰሚ በማጣቱ በወሰደው እራሱን የማቃጠል እርምጃን ተከትሎ ከቱኒዝያ አልፎ የአረብ ጸደይ(Arab Spring) በሚል ስያሜ ጠቅላላ የአረብ አገራትን በለውጥ ነውጥ ውስጥ የከተተ መሆኑን ያዬነው የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው።የሕዝብ ተቃውሞን ተከትሎ የሚመጣ የስርዓት ለውጥ ሲጀመር ከትንሽና በተወሰነ ከባቢ እንደሆነ በአገራችንም የለውጥ ታሪክ የታዘብነው ነው።አይጀመር እንጂ ከተጀመረ ሊቋቋመው የሚችል ምድራዊ ሃይል አይኖርም።ምንም እንኳን ለጊዜው በሃይል ሚዛን ወይም በንቅናቄው ዙሪያ በመጀመሪያው ላይ በሚከሰቱ ድክመቶች ምክንያት ሊያግዱት ቢቻልም የሕዝብን ልብ ግን አንዴ ከሸፈተ ወደ ቦታው ለመመለስ አይቻልም፤ይበልጥ ከስህተቱ እዬተማረ ዓላማውን ከግቡ ያደርሳል።ከዚህ የታሪክ ሃቅ ለመማር የማይችሉት ቢኖሩ ህሊናቸው በእብሪትና በማን አህሎኝነት የታወሩ፣በጥቅምና በአልጠግብ ባይነት የሰከሩ አምባገነኖች ብቻ ናቸው።የአምባ ገነኖች የመጨረሻ መድረሻ ፌርማታቸው ውድቀትና ያንንም ተከትሎ የሚደርስባቸው ቅጣት መሆኑን ቢረዱትም ከዚያ ለመዳን ለሕዝቡ ጥያቄ መልስ ከመስጠት ይልቅ የሰፈረባቸው እራስ ወዳድነት በሽታ በያዙት የቁልቁለት መንገድን የሙጥኝ ብለው እንዲቀጥሉበት አድርጓቸዋል።ለዚያም ነው የሞት የሽረት የመጨረሻ ሙከራቸውን ለማድረግ ያለ ሃይላቸውን አሰልፈው በሕዝቡ ላይ ለመዝመት ከውሳኔ ላይ የደረሱት።በዋና ጠላትነት የፈረጁትን፣ስጋትና ብርክ የለቀቀባቸውን የሕዝባዊ ሃይል ፋኖን ለማጥፋት ሁለገብ ዘመቻ ከፍተውበታል።ፋኖንም ብቻ ሳይሆን፣በጸና ኢትዮጵያዊነት ማማ ላይ የቆሙትን፣ለሥርዓቱ የማያጎበድዱትን እዬለቀሙ በመግደልና በማፈን ተግባር ላይ ከተሰማሩ ውሎ ያደረ ቢሆንም ከሰሞኑ ይህንን እኩይ ተግባር በስፋት ቀጥለውበታል።

የመንግሥት እርካብ የተቆናጠጠው የኦሮሙማው ቡድንና በዬክልል ተብዬው የጎሳ በረት በምስለኔነት የተሰዬሙት ተከታዮቹ ለሚያደርጉት ዘረፋና አገር የማጥፋት ዓላማ እንቅፋት በሆነው በአማራ ማህበረሰብና የሱም መከታ በሆነው ፋኖና ልዩ ሃይል አባላት ላይ የሚደረገው ዘመቻ በስፋት ቀጥሏል፣

ለፋኖ አጋዥና ተባባሪ ናቸው የሚሉትንም ነጋዴ፣ምሑር፣ጋዜጠኛ፣ወጣት፣ተማሪና መምህራን፣የጦር ሹማምንትና ወታደራዊ አባላት ሁሉንም  በመግደልና በማፈን ላይ ተሰማርተዋል።ይህ እብሪታዊ ሙከራቸው ግን ሕዝቡን ሰጥ ለጥ አላደረገውም።ፋኖ ልጆቹ ሲነኩ ሕዝቡ አውራው እንደተነካበት ንብ ተነስቶ ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን ሃይሉን ተጠቅሞ አደብ እንዲገዙ አድርጓቸዋል፤የታሰሩትንም አስለቅቋል።በመርሳ፣በዋግና በሞጣ የተከሰተው ተኩስ ያካተተው ሕዝባዊ ተቃውሞና እርምጃ ለዚያ ማረጋገጫዎች ናቸው።ለእብሪተኛው የኦነግ መራሹ መንግሥትና ለተላላኪው የባእዴን አባላት ግን ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አላደረጋቸውም፤በአጥፍቶ መጥፋቱ ጉዞ ቀጥለውበታል።ከሰሞኑ የአማራው ልዩ ሃይል ዋና አዛዥ በነበረው በብርጋዴር ጀነራል ተፈራ ማሞ ላይ የተፈጸመው የአፈና እርምጃ በወንጀል ተራራው ጫፍ ላይ የተጨመረ  ግን በለውጡ ጉዞ ጉልህ ሚና የሚኖረው ጠብታ እንጂ የመጀመሪያና የመጨረሻው አይደለም።ጀነራሉን ከአዲስ አበባ አውራ መንገድ ላይ በታጠቁ የመንግሥት የአፋኝ ሃይሎች አፍኖ በሄሊኮፕተር ባሕርዳር ወስዶ የማሰሩ ትእዛዝ የመጣው ከአብይ አህመድ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።የታፈኑ ሰዎች የተወሰዱበት ሳይታወቅ ከእይታ መሰወርም የሚቻለው የመንግሥት ጠንካራ ምስጢራዊ ሰንሰለት የሚፈጸም ወንጀል ስለሆነ እንጂ በተራ አሸባሪ ደረጃ የሚከናወን ሆኖ አይደለም።ከእርምጃው በፊትና በኋላ የሚሰራጩት የመንግሥት ዛቻና መግለጫዎችም የዚሁ አፈና ማረጋገጫዎች ናቸው። ከጀነራል ተፈራ ማሞ በፊትም ሆነ በኋላ ብዙ ለሃቅ የቆሙ፣በኢትዮጵያዊነታቸው የማይደራደሩ በተለይም ለአማራው ማህበረሰብ ስቃይና መከራ የሚናገሩ ደፋር አገር ወዳዶች የአፈናው ሰለባ ሆነዋል፤እየሆኑም ነው።በስውር ታፍነው ዬት እንደገቡ ያልታወቁትን ብዙሃን ቤተሰቦች ላይ የደረሰውን ጥልቅ ሃዘን  ስናስብ፣ታዋቂው አዛውንት ጋዜጠኛ ታዲዮስ ታንቱ ሳይቀሩ ከመንገድ ላይ ታፍነው ለዳግም እስራት መዳረጋቸውን ስንሰማ በቤተሰባቸው ላይ ያደረሰውን  ተደጋጋሚ ሃዘንና ሰቆቃ እኛም እንጋራለን።አፈናው በዚህ ብቻ አይቆምም፤አሁንም ምህዳሩን አስፍቷል። የባልደራስ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች በዬቦታው እዬታደኑ ነው።በቀጣዩ ውጋት የሆኑበትን ጋዜጠኞችንና የፖለቲካ ተንታኞችን እንደ መስከረም አበራ፣ማእዛ ሞሃመድንና ሌሎቹንም የማፈኑ ተግባር ላለመቀጠሉ ዋስትና የለም።ማነህ ባለሳምንት ነው።

የኦነግ-ኦሕዴድ ብልጽግና አፋኝ ቡድን እያፈነ የሚያሰቃዬው በራሱና ባእዴን በተባለው አሽከር ድርጅት ድብቅ ቦታ መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ የሕዝቡን ጻረ ባእዴንነት ይበልጥ እያሳደገው መጥቷል። በአማራው ስም ሥልጣን ወንበር ላይ የተኮፈሰው የኦነግ መራሹ ኦሕዴድ አሽከር ድርጅት እንኳንስ እራሱ በሚያካሂደው ጻረ ሕዝብ ተግባር ይቅርና በአማራው ላይ ሌሎች የሚፈጽሙትን ስቃይና መከራ ማስቆም ቀርቶ ባለመቃወሙ፤ይባስ ብሎም ለአድራጎታቸው ካባ እዬሸለመ በርቱ ማለቱ በግንባር ቀደምነት ተጠያቂ ያደርገዋል።

ይህ እንደምሳር እጀታ የሚጠቀሙበት ከአማራው የተቆረጠ ሆድ አደር፣ሌቦችና ባንዳዎች የተሰበሰቡበት፣ ለመጣ ለሄደው የሚያገለግል ብአዴን የተባለ ምንደኛ  ላለፉት 31 ዓመታት በአማራው ማህበረሰብ ላይና በአጠቃላይ በኢትዮጵያውያን ላይ ለሚፈጸመው በደልና አገር የማፍረስ ተልእኮ ሁነኛ መሣሪያ በመሆን ያገለገለና በማገልገልም ላይ ያለ ድርጅት ነው።ለ27 ዓመታት ለወያኔ መራሹ ኢሕአዴግ የጀርባ አጥንት በመሆን፣ ላለፉት 4 ዓመታት ደግሞ በዬጊዜው ስሙን ለሚለዋውጥ ለኦነግ-ኦሕዴድ መራሹ ቡድን ተላላኪ በመሆን አሽከርነቱን በግልጽ ያሳዬ ከንቱና ከሃዲ ከዚያም አልፎ የሌባ ቡድን የተሰበሰበበት መሆኑን በስርቆት ተግባሩ አሳይቷል።ለፈጸመው ወንጀል ላለመጠዬቅና ፍትሕን ለማፈን ሲል የሕዝቡን ተቃውሞና የለውጥ ትግል ለማጨናገፍ መፈለጉ ህይወቱን ከማትረፍና ከሚደርስበት ቅጣት ለማምለጥ ከሚደረግ ሙከራ ጋር የተያያዘ ነው።ይዋል ይደር እንጂ ከፍትሕ የሚያመልጡበት ዕድሉ የመነመነና ጀንበሯ እዬጠለቀችባቸው ለመሆኑ የተነሳሳው ሕዝባዊ እምቢባይነት አመላካች ነው። የክልሉ ምስለኔ የሆነው የባእዴኑ ተጠሪ ግን ፋኖን የምንሾመውና

እውቅና የሰጠነው አካል እንጂ የምናሳድደው አይደለም ሲል አይናችሁን ጨፍኑ ላታላችሁ የሚል የቂል ጨዋታውን አሰምቷል።ይሉሽን ባልሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ብለን ከማለፍ በቀር ለዚህ ጅላጅል ተላላኪ የሚታለልለት አይኖርም።በዚሁ ከንቱ የክልሉ መሪ እውቅናና ትብብር ኦነግ ኦሕዴድ የታጠቁ ነፍሰገዳዮቹን በአማራው ክልል ሲያሰማራ ተባብሮ እዬጠቆመና መንገድ እዬመራ የአማራ ልጆችን ፋኖንና ልዩሃይሉን በማደን ላይ ነው።ጥቂት ሆድ አደር አማሮችን ከፊት አሰልፎ በተለያዩ ቦታዎች በሸዋ፣በወሎ፣በጎንደርና ጎጃም ፋኖን በመከበብና በማጥቃት ከባቢውን የጦር ቀጠና አድርጎታል።ፋኖን አናስነካም ብለው የሚጠብቁትን ያልታጠቁ ወጣቶች ካለርህራሄ በጥይት ደብድቧቸዋል። ብዙዎች ሞተው ብዙዎችም ቆስለዋል።በደሴ፤በወልድያ፣በጎጃም--በተደረገ አሰሳና ዘመቻ ብዙዎች ረግፈዋል። የወራሪ ሃይሉም አባላት የጥይት እራት ሆነው ቀርተዋል።ወረራውን በመቃወም ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ተቃውሞውን ገልጿል፣በመግለጽም ላይ ነው።ይህ ሁሉ የሚያሳዬው ሕዝባዊ አመጽ መጀመሩን ነው።

መንግሥት ተብዬው አገር አጥፊ ቡድን ሕግና ሰላም ለማስከበር በሚል ሽፋን የሚወስደው ሕገወጥ እርምጃ አገራችንን ሰላም አልባ እያደረጋት ነው።ለነሱ ሰላም ማለት፣ሕግ ማክበር ማለት ድምጹን አጥፍቶና ለጥ ሰጥ ብሎ መገዛት ማለት ነው።ሁሉም አምባ ገነኖች የሕዝብ ተቃውሞ ሲነሳ ሰላም ደፈረሰ ይላሉ፤ሲገሉና ሲያስሩ ግን የሚሰጡት ሽፋን ሰላም ማስከበር የሚል ነው። “ሰላም ሆይ በስምሽ ስንት ግፍ ተሠራ!” የሚለው አባባል የዚሁ ድርጊት ገላጭ ነው።

ቀደም ሲል በዚሁ በአገር እንዴት ሰነበተች መልእክታችን ሁኔታውን መርምረን እንደጠቆምነውና በታዋቂው በጥቁር አሜሪካዊው ድምጻዊ ዘፋኝ በሳም ኩክ የጥቁሮችን የመከራ ዘመን አስመልክቶ ከስልሳ ዓመት በፊት ለውጥ አይቀርም፣ይመጣል የሚለውን እንጉርጉሮ አባሪ አድርገን እስከነይዘቱ ተርጉመን ያቀረብነው መልእክት በአገራችንም ለውጥ እንደማይቀር በማሰብ ያቀረብነው ዘገባ አሁን በገሃድ በመታዬት ላይ ነው።አሁንም እንላለን ኤ ቸንጅ ጎና ካም፣(A Change Gonna come) ለውጥ አይቀሬ ነው።ይመጣል!!እዬመጣም ነው።ለዚያ ወሳኝ ሕዝባዊ ትግል ስንቅን መሰነቅ፣ትጥቅን መታጠቅ የግድ ይላል።አንድነት ያለው አመራር ፈጥሮ ትግሉን በብቃት መምራት ለድሉ ዋስትና ነው የሚለው የተለመደውን መልእክታችንን እንደግማለን።ጀነራል ተፈራ ማሞ ትርፍ አንጀት ብሎ የሰዬመውን ቡድን በእኛ በኩል የአንጀት ካንሰር ብለነዋል።ትርፍ አንጀትም ሆነ ካንሰር ተቆርጦ ካልተጣለ በጤና መኖር አይቻልም፤አደጋው የከፋ ይሆናል።ስለሆነም ያገራችንን አንድነትና ሰላም ብሎም እድገት፣ የሕዝቡን መስተጋብርና አብሮነት፣የምንመኛትን የተሻለች ኢትዮጵያን ለማረጋገጥ የግድ በሥልጣን ላይ ያለውን የጎሰኞች ስርዓትና አስተሳሰብ ነቅቅሎ መጣል የግድ ይላል።

እንደ እብድ ውሻ በያቅጣጫው መንከስ ልማድ የሆነበት የኦነግ -ኦሕዴድ ተስፋፊ ቡድን የሚያደርገው የግዛት መስፋፋትና መተናኮል በአማራው ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከሰሞኑም ከሲዳማ ክልል ጋር እሰጥ አገባ ጀምሯል፤ ከቃላት የማስጠንቀቂያና ፉከራም ባለፈ በጦር መሣሪያ የታጀበ ወረራና ግጭት አካሂዷል፤ከ10 በላይ ሰዎችም ተገለዋል።በዚሁ በደቡብ የአማሮ ወረዳ ሁለት እረኛ ልጆች በመስክ ላይ በኦነግ ወራሪ ቡድን በጥይት ተገለዋል።ከዚህ ሌላው ሊማር የሚገባው ቢኖር የኦሮሙማው ቡድን ኦሮሚያ የተባለ አገር ለመፍጠር በሚያደርገው ሙከራ በያቅጣጫው የግዛት ወሰኑን ለማስፋት ከሁሉም ጋር ጦር እንደሚማዘዝ ነው።ከዚህም በፊት ከሶማሊያ፣ከአፋር፣ከጋምቤላ ክልሎች ጋር ተመሳሳይ ጦርነቶች ማድረጉ አይረሳም።ይህ ማንም ብቻውን በሰላም ሊኖር እንደማይችል ማሳያ ነው። ሁሉም በሰላም ሊኖር የሚችለው፣ ወያኔ የሰጠውን ክልል የተባለ ጠባብ በረት ሰብሮ በአንድ አገራዊ ቁመና፣በኢትዮጵያዊነት የተቀማውን የትልቅ አገር ባለቤትነቱን መልሶ ሲወስድና በጠንካራ አንድነት ክፍለሃገሩን ሲመራ ነው።የወያኔና የኦነግ -ኦሕዴድ የጋራ ዓላማ ኢትዮጵያን አጥፍቶ በውስጧ ያሉትን

ነጣጥሎ መቀራመት ነው።ለዚያ እኩይ ዓላማ መሣሪያና የተጋለጠ ላለመሆን ሁሉም በጋራ መሰለፍ ይኖርበታል።

ከሰሞኑ ከታዘብናቸው መካከል ከውስጡ በተጨማሪ በውጭ ሃይሎች ዙሪያ የሚደረገውን ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ የተቀናጀ ዘመቻ ታዝበናል።የጎረቤት ሱዳን ወታደራዊ መንግሥት ትንኮሳውን የቀጠለበት ሲሆን የወያኔን ተዋጊ በማሰልጠንና በማስታጠቅ ወደ ጦር ሜዳ በከሰላ በኩል ማሰማራቱ ተሰምቷል፣ግብጽም የአሜሪካንን መንግሥት በግድቡ ላይ ጣልቃ እንዲገባ በመወትወት ላይ ትገኛለች፤ የባይደን አመራርም እንደ አገር በቀሉ ባእዴን  ከሙተባበር እንደማይመለስ የሚያሳዩ የተግባር ማስረጃዎች ታይተዋል።በሶማሊያ በኩል አልሸባብን ለመዋጋት በሚል ሽፋን 500 ወታደሮች የመላኩን ነገር አዲስ ከተመረጠው የሶማሌ ፕሬዚዴንት የድጋፍ መልእክት ጋር አያይዘን ስንፈትሸው የሂደቱን ትስስር ያመላክታል። የኬንያ መንግሥትም በበኩሉ የጸጥታ ስጋት አለብኝ በሚል ሽፋን በኢትዮ ኬንያ ድንበር በሆነው በሞያኔ ጠረፍ ላይ ወታደሮቿን ማሰፈሯን ይፋ አድርጋለች፣ከዚችው ከኬንያ ሳንወጣ የተሰማው ነገር በዋና ከተማዋ በናይሮቢ የኦሕዴዱ መሪ  አክራሪው ጁዋር ሞሃመድ ከአሜሪካ የስለላ ተቋም ከሲ አይ ኤ(CIA) አባል ጋር መገናኘቱ ታውቋል።ወያኔና ኦነግም እንዳቅማቸው በመንግሥት ደረጃ ለአዲሱ የሶማሌ ፕሬዚዳንት የድጋፍ መልእክት መላካቸውን ታዝበናል። የኦነግ ኦሕዴዱም መሪ አብይ አህመድም እንዲሁ።አዲሱ ፕሬዚዴንት በቀድሞም ጊዜ የዚችው የፈረደባት ሶማሊያ ፕሬዚዴንት የነበረና ለወያኔ ልዩ ፍቅርና ግንኙነት እንደነበረው ይታመናል።ከአሜሪካኖቹ የሴራ ትብትብ ሳንወጣ በሚቆጣጠሩት የተባበሩት መንግሥታት በኩል የሰብአዊ እርዳታ አስመስሎ ለወያኔ የጦር መሳሪያና የፖለቲካ ድጋፍ ያለው ጫና በማድረግ ላይ ሳይቆም በነሱው በሚሽከረከረው የዓለም ባንክና የአይ ኤም ኤፍ (IMF) በኩል የሚሰጠውንም የገንዘብ ብድርና እርዳታ፣መሸንገያ ቢባል ይሻላል የፖለቲካ ፍላጎታቸው ማስፈጸሚያ መሣሪያ  አድርገውታል።የአሜሪካ እርዳታ (US Aid)የተባለው ድርጅት የመደበውን ገንዘብም ከወልቃይት ጥያቄ ጋር በማያያዝ ከባቢው ለወያኔ ካልተመለሰ በቀር እንደማይሰጥ ሳማንታ ፓወር የተባለችው ሃላፊ በይፋ ገልጻለች።የምዕራባውያንም ሆኑ በተለይም የአሜሪካኖች ድጋፍ ለሰማይ ቤት የሚያደርጉት ሰብአዊነት ሳይሆን ለሚፈልጉት የአሽከርነት ሙያ መደለያ እንደሆነ አውቆ እራስን የመቻሉ ስሜትና ፍላጎት ማሳደሩ የነጻነትና የነጻ አገር ባለቤት ያደርጋል።መከበር በልመናና በበታችነት የሚገኝ ሳይሆን በራስ መተማመንና በአገር ፍቅር ተባብሮ የመቆም ውጤት ነው።ታሪካቸው ዘረፋና ወረራ ከሆኑ አገሮች በኩል መልካም ነገር አገኛለሁ ብሎ ማሰብ የዓለምን የጦርነቶች ታሪክ ካለማወቅ ወይም ከመካድ  የመነጨ አድር ባይነት ወይም ባንዳነት ነው።የአፍሪካ አገሮች በአምባ ገነኖችና በኩዴታ የሚናጡት በነዚሁ የውጭ ምዕራባውያን በሚጠነሰስ ሴራ ነው።የፈለጉትን ይተክላሉ ዘነፍ ሲል ደግሞ ነቅለው በሌላ አገልጋይ ይተካሉ።የወያኔን አገር የማጥፋት ዓላማ እንደ በጎ በማዬት ድጋፋቸውን የሚሰጡት ኢትዮጵያንና ኤርትራን ለማንበርከክና በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ እንደሆነ የማያውቅ አለ ብለን አንገምትም።አንድ በመስጠት አሥር የመውሰድ ልማድና ፍላጎት እንዳላቸውም የሚዘነጋ አለ ብለን አናስብም።ብዙዎች የተሳተፉበትና አብይ አህመድ የቀጨው የኖ ሞር(No More) እንቅስቃሴ የዚያ የሕዝብ እምቢተኛነት ነጸብራቅ ነው።

ለኢትዮጵያም ሆነ ለኤርትራ ሕዝብ ሰላምና የወደፊት እድገት እንዲሁም የውጩን ትንኮሳ ለመቋቋም የሚረዳው አንዱ ብቸኛ መንገድ ሁለቱ አገሮች በፌዴሬሽን ቢጣመሩ ነው።ለዘመናት አብረው ለኖሩ ፣ በብዙ መስተጋብሮች ለተሳሰሩ ሕዝቦች የቅርብ ጊዜ መለያዬት እንቅፋት ይሆናል ብለን አናስብም። ከሚለያዩበት ይልቅ የሚቀራረቡበትና የሚያስተሳስራቸው ድርና ማግ ብዙ ነው።በውጭ ግንኙነት፣ በመከላከያ፣በኤኮኖሚ፣በባሕልና የትምህርት ዘርፍ አብሮ በመሰለፍና በመተባበር እንዲሁም የሁለቱም አገር ተወላጅ በነጻ የመንቀሳቀስና የመኖር፣የመሥራት መብቱ ቢከበርለት ለሁለቱ አገሮች ብቻም ሳይሆን ለቀጠናው ሰላምና እድገት ወሳኝ ይሆናል።የወያኔና መሰሎቹም ሴራ ይከሽፋል።ከሁሉም በላይ

ግን በኢትዮጵያ የሰፈነውን የጎሳና ክልል ፌዴራሊዝም ለማሶገድ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል።ምክንያቱም የሁለት አገሮች ማእከላዊ መንግሥታት ግንኙነትና ፌዴራሊዝም እንጂ የሰማንያ ጎሳና የአሥራ አንድ ክልሎች መንግሥታት ግንኙነትና ፌዴራሊዝም ስለማይሆን ነው።

ግራ የተጋባው የኦነግ ኦሕዴድ መራሹ አካል የሆነው የአዲስ አበባው አስተዳደር የሕዝቡን የተቃውሞ አቅጣጫ ለማሳትና ለመዝረፍ የአዲስ አበባ ከተማ ህንጻዎች በሙሉ ግራጫ ቀለም እንዲቀቡ ሲል መመሪያ ማውጣቱ ተሰምቷል፣ይህ መሳቂያና ማፈሪያ የሆነ ውሳኔ ለምን እንዳስፈለገ የተሰጠ ሳይንሳዊና የሚያሳምን ምክንያት የለም።ባለፈው ጊዜ የአዲስ አበባን ማዘጋጃቤት እድሳት ተንተርሶ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ዓይን ያወጣ ዘረፋና ድፍረት ይዘን ወደ አሁኑ ውሳኔ ስንመለከት ከዘረፋ የተለዬ ትርጉም እናጣለታለን።በአንዱ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የቀለም እድሳት ምክንያት ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ወጣ ማለቱን ስንሰማ በአሁኑ የከተማዋ ሕንጻዎች ላይ ሊወጣ የሚችለው ገንዘብ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ሲያስቡት ይዘገንናል።ሕዝብ የሚልስ የሚቀምሰው አጥቶ በርሃብና ችግር በሚቆላበትና የውጭ አገር እርዳታ ያለህ በሚልበት ከተማ ውስጥ ይህንን ያክል ድፍረትና ሃላፊነት የጎደለው የሌቦች ውሳኔ መስማትን ያህል የሚያም በሽታ አይኖርም፤ኢትዮጵያን የሚያክል ትልቅና ታሪካዊ አገር በምን አይነት የሌቦችና ግዴለሾች መዳፍ ሥር የወደቀች፣ስለከተማ ምንም አይነት እውቀት በሌላቸው ከተማ ጠሌዎች የ8 ሚሊዮን ሕዝብ መኖሪያ፣የ 120 ሚሊዮን ሕዝብ መናገሻ ከተማ፣የአፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ እንደ ዝባዝንኬ ዕቃ ተደርጋ መጫወቻ ስትሆን ማዬትን የመሰለ ቅሌት የለም።በነዚህም አይነቶቹ ለሚመራ ሕዝብ ትልቅ ሃፍረት ነው።

የአስተዳደሩ ውሳኔ ከተማዋን ዋጋቢስና ትኩረት አልባ ከማድረጉ ከኦነጉ ውሳኔ የተለዬ አይደለም። ኦነጎቹ አዲስ አበባን ዋጋና ትርጉመቢስ ከተማ እናደርጋታለን ያሉትን ለመፈጸም ፣የከባድ ክረምት ምልክት የሆነውን ግራጫ ቀለም መምረጣቸው ያለምክንያት አይደለም።አብይ አህመድም የድርጅቱን የብልጽግና አባላት በግራጫና በጥቁር ቀለም ቀብቶ ለማጥቃት መመደቡን ያዬነው ስለሆነ አይደንቀንም። የአስተዳደሩም አባላት ያንን ተከትለው ግራጫ ቀለም ቀብቶ የከተማዋን ገጽ ለማጥፋትና በጭጋግና ዳመና ድባብ የምትጠላና የምታስፈራ ከተማ የማድረግ ህሳቤ ይመስላል። ግራጫ ቀለም ቀርቶ እንደ እሬቻ ዛፍ ሁሉንም ህንጻ ቅቤ ቀብተው ቢሳለሙት አይደንቀንም።በማን አገርና በዬትኛውስ ከተማ ቤትና ሕንጻ አንድ አይነት ለዚያውም የመከራ ትርጉም ባለው ቀፋፊ ግራጫ ቀለም ይለቀለቃል?የቀለሙ ጉዳይ የተነሳው የሕዝቡን የትግል ስሜት ለማስለወጥ ብሎም ለዘረፋ ታስቦ እንጂ ለከተማዋ ውበትና ለነዋሪው ምቾት ታስቦ አይደለም።መረጃው በብዛት ወጥቶ ተቃውሞ ሲነሳ የከተማዋ አስተዳደር ብቅ ብሎ ቀለም ለመቀባት አልተወሰነም ግን ስለከተማዋ ቤቶች ምን አይነት ቀለም ይቀቡ የሚል ውይይት ተካሂዷል ሲል እራሱን በራሱ አጋልጧል።በተቃዋሚውም በኩል ቀለም ሊቀቡ ነው ተባለ እንጂ ቀለም ቀቡ አልተባለም።

ለድፍረቱ ገደብ የሌለው አብይ ሥልጣኑን እንደወሰደ ማግስት የአራት ኪሎን ታሪካዊ ቤተመንግሥት አድሳለሁ ብሎ ያባከነው የብዙ ቢሊዮን ብር ወጭ ጠያቂ ባለመኖሩ በመዝናናትና ማን አለብኝነት ስሜት አሁን ደግሞ ሕዝብ የሚልሰው የሚቀምሰው አጥቶ የእርዳታ ያለህ እያ| ሲጮህ ጆሮውን በጥጥ ደፍኖ ከራስ በላይ ንፋስ በሚል እብሪት ብዙ ዜጎችን ከኖሩበት ቦታ በሃይል አስነስቶ በ49 ቢሊዮን ብር አዲስ ቤተመንግሥት እሠራለሁ ብሎ ሲነሳ ተቃውሞ አለመውጣት ከተማዋ ባለቤት የሌላት መሆኗን ያሳያል። ወጣም ወረደም ላገራችን ያለው መፍትሔ የተደራጀ ሕዝባዊ አመጽ አካሂዶ ይህንን የጎሳ ሥርዓት ከነግታንግቱ ማሶገድ ነው፤ለዚያም የጋራ ግንባርና አመራር መፍጠር ግድ ይላል።

የጋራ ግንባር አሁኑኑ! ሕዝባዊ አመጹ ይፋፋም!! ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘላለም ትኑር!!!